# የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ባህላዊ አለባበስና አጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች

‘በምንታምር ልንገርህ[2] ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

## አጽህሮተ ጥናት

ቁሳዊ ባህል የሚባለው የፎክሎር ዘርፍ አንድ ማህበረሰብ ለመገልገያነት የሚሰራቸው፣በአይን የሚታዩ የሚዳሰሱና በተጨባጭ የሚገኙ የተለያዩ ቁሶችን መግለጫ ነው።ይህ የፎክሎር ዘርፍ ስለማህበረሰቡ አጠቃላይ ጉዳይ በተጨባጭ የሚያሳውቅ ነው።የአንድ ማህበረሰብ ቁሳዊ ባህል ዕለት ከዕለት የኑሮ መገልገያነት ባለፈ መንፈሳዊ ሃብቱን ለማስተላለፍ፣ ለማስቀመጥና ለመጠበቅ የሚጠቀምበት አይነተኛ መንገድ ነው፡፡ የሰው ልጅ በዕለት ከዕለት የኑሮ ሂደቱ ከሚጠቀምባቸው ቁሳዊ ባህሎች ዋነኞቹ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ናቸው። ልክ እንደ ቋንቋ ሁሉ በባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡ ውስጥ የሚገኙት ትዕምርቶች የአንድን ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብ ማንነት ከመግለፅ፣ ከማሳየትና ከማሳወቅ አንፃር ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ስለሆነም የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በገጠራማው አካባቢ የሚኖረው የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ አካላዊ ገፅታ ማሳየትና ትዕምርታዊ ፋይዳ መተንተን ነው። ይህን ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስ ቀዳማይና ካዕላይ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል።በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ንድፈ ሃሳቦች የተቃኙ ሲሆን በገላጭና ተርጓሚ እንዲሁም አልባሳቱ እና ጌጣጌጡ ከሚውሉበት ወይም ከሚጌጡበት የሰውነት ክፍል አንፃር ተከፋፍለው ተተንትነው ቀርበዋል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በርካታ አልባሳትና ጌጣጌጥ አገልግሎት ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። እነዚህ አልባሳትና ጌጣጌጥ ከጥጥ፣ የፋብሪካ ውጤቶች ከሆኑ ጨርቆች፣ ከብር፣ ከመዳብ፣ ከቆርቆሮና ከዶቃ(ጨሌ)፣ ከቆዳና ከክር የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ በጥናቱ ባህላዊ አልባሳቱ እና ጌጦቹ ከመለበስ እና ከማስጌጥ ባለፈ በአልባሳቱና በጌጦቹ ውስጥ የሚገኙ ትዕምርቶች የማህበረሰቡ የማንነትና የእድሜን መግለጫ፣ የህይወት ምዕራፍ ሽግግር ማሳያ፣የህይወት ፍልስፍና

---

[2]በደብረማርቆስዩኒቨርሲቲየኢትዮጵያቋንቋዎችናሥነ-ጽሁፍ (አማርኛ) ትምህርትክፍልመምህርት፣ስልክቁጥር 0910042426፣ E-mail: lmintamir@gmail.com, መስከረም/2012 ዓ.ም

ማንፀባረቂያ፣የማህበራዊ ደረጃና የማህበራዊ ሁኔታ መለኪያ መሆናቸው የሚያመላክቱ እንደሆኑ ተደርሶበታል። እንዲሁም ባህላዊ አልባሳቱና ጌጦች ከፍተኛ ማህበራዊ ትስስር እንደሚፈጥሩና በማህበረሰቡና በለባሹ መካከል ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ተግባቦትን የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑ ተረጋግጧል። በአጠቃላይ በጥናቱ የተዳሰሱት አልባሳትና ጌጣጌጥ ከገላ መሸፈኛነትና ማስጌያጫነት በተጨማሪ ትዕምርታዊ ውክልናቸው ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እና መንፈሳዊ መግባቢያ ያላቸው በመሆኑ የማህበረሰቡን እሴቶች የሚገልፁ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

*ወሳኝ ቃላት* (Key Words): *ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ ጌጣጌጦች፣ ምስራቅ ጎጃም፣ኢትዮጵያ (Folk Costume, Folk Jewlelry, East Gojjam, Ethiopia)*

## 1. መግቢያ

### *1.1. የጥናቱ ዳራ*

ቁሳዊ ባህል የሚለው ሐረግ አንድ ማህበረሰብ ለመገልገያነት የሚሰራቸው፣በአይን የሚታዩ፣ የሚዳሰሱ እና በተጨባጭ የሚገኙ የተለያዩ ቁሶችን ለመግለፅ የሚጠቅም ስያሜ ነው (Prown,1982)። ይህ የፎክሎር ዘርፍ ስለማህበረሰቡ አጠቃላይ ጉዳይ ወይም ሁኔታ በተጨባጭ የሚያሳውቅና የሚገልጽ ነው (Sims & Stephen, 2005):: Woodward (2007) እንደገለጸው አንድ ማህበረሰብ በዕለት ከዕለት ህይወቱ የሚገለገልባቸው እና የተለያዩ ጉዳዮቹን ማለትም እምነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ አመለካከቱን የሚያንፀባርቅበት ዋነኛ ዘዴው ጉልበቱን፣ ጊዜውን፣ ሃብቱንና እውቀቱን አፍስሶ በሚሰራቸው ቁሶቹ ነው:: ቁሳዊ ባህል የአንድን ማህበረሰብ መንፈሳዊ ሃብቱን ለማስተላለፍ፣ ለማስቀመጥና ለመጠበቅ የሚጠቀምበት አይነተኛ መንገድ ከመሆኑ በተጨማሪ ባህላዊ ገፅታውን የማሳወቅና የመግለጽ ከፍተኛ አቅም ያለው መሆኑን Prown (1982)ገልጿል።

አንድ ማህበረሰብ በዕለት ከዕለት የኑሮ ሂደቱ ከሚጠቀምባቸው ቁሶች መካከል ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ዋነኞቹ ናቸው (Yoder, 1972):: ባህላዊ አልባሳት(Folk Costume) የአንድን ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብ ማንነት ከመግለፅ አንፃር ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ቁሳዊ ባህሎች ናቸው:: ይህን ሀሳብ በተመለከተ Baatshwana(1965)፣Twigg (2007)፣Yoder (1972) እና Wilson (1986) ባህላዊ አልባሳት እንደማንኛውም አልባሳት ሆነው ነገር ግን የተገለጋዩን ማህበረሰብ ማንነት የሚያሳዩ ትእምርቶችን የያዙ እንዲሁም በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦችና በማህበረሰቡ መካከል ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉ ናቸው በማለት አስቀምጠውታል። እንዲሁም አልባሳት ማንነትን በማሳየትም ሆነ በመቀየር ወይም በማጥፋት ረገድ የራሳቸው ድርሻ እንዳላቸው Twigg (2007, ገ.10) አስረድቷል:: አልባሳት ከአካላዊ ገፅታቸው በተጨማሪ በሚይዟቸው ትዕምርቶች አማካኝነት ከሚያስተላልፏቸው ጉልህ መልዕክቶች የመነጨ መሆኑ የሚያሳይ እና ልብስን በማየት የለባሹን ማህበረሰብ ከየትነት እና ባህል መናገር የሚቻልበት አጋጣሚ እንዳለ Lurie(1981) አስረድቷል። Lurie(1981, ገ.5) ሀሳቡን ሲያጠቃልልም “clothes are expressions of identity, one of the perennial means whereby we signal to the social world who and what we are” በማለት የአልባሳትን የማግባባት አቅም ከፍተኛነት አስረድቷል።

በመሆኑም ባህላዊ አልባሳት ስንል አንድ ማህበረሰብ የኔ ብሎ በሚመራበት ባህል ውስጥ በሚታወቁ ትእምርቶች የበለፀጉ፤ በማህበረሰቡ ዘንድ ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉና በሚያስተላልፉት መልዕክትም የተለያዩ ጉዳዮችን ማሳወቅና መግለፅ የሚችሉ ቁሶች መሆናቸውን ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች መረዳት ይቻላል።

ባህላዊ አልባሳት የተለያዩ መልዕክቶችን የማስተላለፍ ከፍተኛ የሆነ ብቃት አላቸው (Wilson, 1986):: Wilson እያይዞም ይህን የሚያደርጉት በተለይ ኢ-ቃላዊ (non verbal) በሆነ መንገድ ነው::

ምክንያቱም አልባሳት ልክ እንደ ቋንቋ ሁሉአንድን ማህበረሰብ ለመግለፅ በዋናነት የሚያገለግሉ በመሆናቸው ነው። በአልባሳቱ ትዕምርቶች አማካኝነት የሚተላለፈው መልዕክት ትርጓሜ የሚወሰነው በለባሹ ማንነት፣ በመለበሻ አጋጣሚው እና በመለበሻ ቦታው ስለሆነ የአልባሳቱ ትዕምርታዊ ፋይዳ የሚመሰረተው በአውድ ላይ ነው (Glacia,2008)።

አልባሳት ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ ከሚያስተላልፉት መልዕክት በተጨማሪ(1) የአካል ክፍሎችን ከተለያዩ ጎጂ ነገሮች የመከላከል፣ (2) ሀፍረትን የመሸፈን፣ (3)አትኩሮትን የመሳብ እና (4) የማስዋብ አራት ተግባራት አሏቸው(Kaiser, 2004)። እንዲሁም አልባሳት የሰውን ልጅ ውጫዊ አካል ከመሸፈን ባለፈ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ ከተለያዩ ክፉ መናፍስት የመከላከል ተግባር እንዳላቸው Gracia (2008) ገልጸታል።

ሌላኛውና የዚህ ጥናት አንዱ አካል የሆነው እና ባህላዊ አልባሳት ሲነሳ አብሮ የሚነሳው ጌጣጌጥም በቁሳዊ ባህል ውስጥ የሚመደብ ነው። ይህ የቁሳዊ ባህል ዓይነት እንደ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ እንዲሁም መኖሪያ አካባቢው መለያየት ሁሉ የሚበጁበት ቁስና ቅርጽም ልዩነት ያሳያል (Clark,1986)። Clark አያይዞም ጌጣጌጥ እንደ አልባሳት ሁሉ ከመዋቢያነት ባለፈ ባላቸው ትዕምርታዊ ፋይዳ የሚጠቀምባቸውን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ማንነት፣ የኑሮ ደረጃ፣ እድሜ እና ፆታ ያመላክታሉ ሲል ገልፆታል።

ቁሳዊ ባህል በሳይንሳዊ ዘዴ ትኩረት ተሰጥቶት መጠናት የጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሆነ (Oestingaard, 2002; Woodward,2007) ገልፀዋል።ከቁሳዊ ባህል መካከል የሆኑት ባህላዊ አልባሳትና ቁሳቁሶች የአንድን ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ ማንነት የመግለፅና የማሳየት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ፋይዳዎች ቢኖሩትም በሀገራችን በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በዚህ ላይ የተከናወኑ የጥናት ዘገባዎች የቅርብ ጊዜ ናቸው።ከእነዚህም ዘገባዎች መካከል ሰይድ (2002) በከሚሴ ከተማ ዙሪያ፣ አመልማል (2004) በአዊ ባንጃ ወረዳ፣ አፀደ (2003) በኮንሶ፣ የኔዓለም (2000) በአርሲ እና ያሬድ (2002) በሰቆጣና አበርገሌ አካባቢዎች የሚገኙ የተለያዩ የሀገራችንን የማህበረሰብ ክፍሎች ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ አጥንተዋል።

ይሁንና በምስራቅ ጎጃም አካባቢ የሚገኙ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ያተኮሩ ጥናቶች በስፋትአይገኙም። አያል (1992) የጎጃም አካባቢን ባህላዊ አልባሳት ስያሜ ቢያጠናውም የአልበሳቱንና የጌጣጌጡን ትዕምርታዊ ውክልናና ማህበራዊ ፋይዳ በጥናቱ አልዳሰሰውም። ስለሆነምይህ ጥናት የተከናወነው የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በባህላዊ አልባሳቱ አማካኝነት የህይወት ፍልስፍናውን እንዴት ይገልፀዋል የሚለው ጉዳይለማመላከትና ዘርፉን ማጥናት ያለውን ጠቀሜታ በማሳየት ወደ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር መድረክ ይበልጥ ለማቅረብ ነው።

*1.2. የምርምርጥያቄዎች*

ይህ ጥናት የተከናወነው ሶስት ዋና ዋና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው። እነዚህም፦

1. የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ምን አይነት ባህላዊ አልባሳትንና ጌጣጌጥን ይጠቀማል?
2. የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡ እንዴት ራሱን ይገልፃል? እና
3. በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ውስጥ የአልባሳቱና የጌጣጌጡ ትዕምርት ምን ይመስላል? ናቸው፡፡

*1.3. የጥናቱዓላማ*

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብን ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ አካላዊ ገፅታ ማሳየትና ትዕምርታዊ ፋይዳ መተንተን ሲሆን የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት።

- ✓ የማህበረሰቡን አልባሳት አካላዊ ገፅታ ማሳየት፤
- ✓ የማህበረሰቡን ጌጣጌጥ አካላዊ ገፅታ ማሳየት፤

- ✓ ማህበረሰቡ ለባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ የሚሰጠውን ቦታ ማሳየት፤
- ✓ ባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡ ባላቸው ትዕምርት የሚያስገኙትን ማህበራዊ ፋይዳ መተንተን።

### 1.4. የጥናቱጠቀሜታ

በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖራቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ✓ የተጠኝዎችን ማህበረሰብ አልበሳትና ጌጣጌጥ ለሌሎች ማህበረሰቦች ያስተዋውቃል።
- ✓ የአንድ ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጥ በዕለት ከዕለት ከሚሰጡት ቁሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ ትዕምርታዊ ውክልና እንዳላቸውም ያስተዋውቃል፡፡
- ✓ በቁሳዊ ባህል በተለይም በባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችላይ ጥልቅ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኝዎች እንደ መነሻ ሀሳብ ሊሆን ይችላል።

### 1.5. የጥናቱወሰን

ይህ ጥናት ምንም እንኳን ዋና ትኩረቱ አልባሳትና ጌጣጌጥ ቢሆኑም ከቁስነታቸው አንፃር ሲታዩ አካላዊ ገፅታቸውን ከመግለፅ ባለፈ የአሰራር ሂደታቸውን አያጠቃልልም:: እንደ (Wilson, 1986) ሃገረሰባዊ አልባሳት (Folk Costume) የተለያዩ ጌጣጌጦችን (Jewelry) የፀጉር አሰራርን (Hair styles) ንቅሳትን (Tattoos) እና የገላ ላይ ጌጦችን (Body decorations) የሚያጠቃልል የጥናት ዘርፍ ቢሆንም ጥናቱን ለማጥናት ካለው ውስብስብነት የተነሳ በዚህ ጥናት ባህላዊ አልበሳትና ጌጣጌጥ ብቻ ተዳሰዋል::

የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ አካባቢዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ያተኮረው በምስራቅ ጎጃም ዞን ውስጥ በሚኖሩ ማህበረሰቦች ላይ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም በዞኑ የከተማ ኗሪዎች እንዳሉ ቢታወቅምይህ ጥናት የተከናወነው በገጠሩ የማህበረሰብ ክፍል አልባሳትና ጌጣጌጥ  ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ጥናትለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ልጆችን አልባሳት እና ጌጣጌጥ አያጠቃልልም።

## 2. የአጠናን ዘዴዎች

### 2.1. የጥናቱ ቅርጽ (ዲዛይን)

ምርምሩ የተከናወነው ገላጭ የጥናት ቅርጽን (ዲዛይንን) በመከተል ነው። ይህን ዲዛይን መከተል ያስፈለገውዲዛኑ (ሀ) የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ለመጠቀም በማስቻሉ፣ (ለ) የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ለመጠቀም ማስቻሉና ለማመሳከሪያነት (Triangulation) አመች በመሆኑ እና (ሐ) ገላጭ መረጃዎችን ለመተንተና ለተርጎም አመች በመሆኑ ነው።

### 2.2. መካነ ጥናት

ይህ ጥናት የተከናወነው በምስራቅ ጎጃም ዞን ሲሆን ዞኑ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በአማራ ክልል ይገኛል። አብዛኛው የዞኑ ማህበረሰቦች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆኑ እ.ኤ.አ በ2007 በተደረገው የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ሪፖርት 2,613,835 (በከተማ= 372,264 እና በገጠር= 2,241,571) ህዝብ ይኖራል (CSA, 2007)። ዞኑ በ18 ወረዳዎች የተከፋፈለ ሲሆን አብዛኛው ህዝብ በገጠር አካባቢ ይገኛል። ስለሆነም ይህ ጥናት የተከናወነው በገጠሩ የዞኑ አካባቢዎች በሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ነው። ምክንያቱም በተደረገው የዳሰሳ ጥናትየከተማ ነዋሪው ማህበረሰብ ከራሱ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ይልቅ በሎሎች አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው፡፡

*2.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች*

የጥናቱ አካባይ (Population) በዞኑ 18ቱም ወረዳዎች በገጠር የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው። የጥናቱን ተሳታፊዎች ለመምረጥ በአጠቃላይ ባለሁለት ዳረጃ (Two-stage) (ያለው፣ 1998) ንሞና ዘዴ ተግባር ላይ የዋለ ሲሆን (ስዕል 1) ከዚህ አካባይ ውስጥ አምስት ወረዳዎች (እነማይ፣ ስናን፣ ባሶሊበን፣ ደብረ ኤልያስ እና ጎዛምን) የተመረጡ ሲሆን እነዚህ ወረዳዎች የተመረጡት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ነው። እነዚህን ወረዳዎች ለመምረጥ የዓላማ ተኮር ንሞና ተግባራዊ የተደረገው በወረዳዎቹ የሚገኙት ማህበረሰቦች የሚኖሩት በተለያየ መልክዓ-ምድራዊ ገጽታ ላይ በመሆኑ የሚገለገሉባቸው አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዲሁ ሊለያዩ ይችላሉ በሚል መነሻ ሃሳብ ነው (Yoder, 1972)።

ለዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው በእነዚህ ወረዳዎች ከሚኖሩ 49 የአልባሳቱና ጌጣጌጡ ተገልጋዮች፣ ሸማ ሰሪዎች እና ጌጣጌጥ ሰሪዎች ነው። ከ49 ሰዎች መካከል 17ቱ በቃለ መጠይቅ 24ቱ በቡድን ውይይት መረጃ በመስጠት የተሳተፉ ሲሆን የቀሩት 8ቱ ሰዎች ቁልፍ ጠቋሚ በመሆን አገልግለዋል፡፡ እነዚህ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተመረጡት ዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴን በመጠቀም ሲሆን (ሀ) ስለባህላዊ አልባሳትሰፊ እውቀት ያላቸው እና (ለ) የአልባሳቱና ጌጣጌጡ ተገልጋዩች እንዲሁም ሰሪዎች የሚሉ መስፈርቶችን በመጠቀም።


*2.4. የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴዎች*

የዚህን ጥናት ቀዳማይ እና ካዕላይ የመረጃ አይነቶችን ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ እና የቡድን ተኮር ውይይቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል።

**ሀ) ምልከታ**

በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጥናቱ ተሳታፊዎች አልባሳት እና ጌጣጌጥ አይነት እና አካላዊ ገፅታ ለመመልከት እንዲሁም የማህበረሰቡ የእርስበ እርስ መስተጋብር በቤተ እምነቶች፣ በገበያ ቦታዎች፣ በመኖሪያመንደሮች እና የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመገኘት ለማየት ተችሏል::

ምልከታው ሲከናወን የፎቶ ምስሎች እንዲሁም የፅሁፍ ማስታወሻዎች ተይዘዋል። የአጠኝዋ መኖር በተሳታፊዎች ላይ አላስፈላጊ ተጽእኖ የሚፈጥርባቸውን ሁኔታዎች ለመቀነስ ሲባል መረጃዎች ሲሰበሰቡ አጥኝዋ ዳር ቁሞ ተመልካች (Non-participant observer) ለመሆን ጥረት አድርጋለች (ያለው፣ 1998)።




የጥናቱ ናሙና (Sample)

| የተሳታፊዎች ምድብ | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ለባሾች | ወንድ | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 13 |
| | ሴት | 6 | 4 | 5 | 6 | 7 | 28 |
| ሸማ ሰሪ | | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 6 |
| ጌጣጌጥ ሰሪ | | - | 1 | - | - | 1 | 2 |
| **ድምር** | | **10** | **8** | **9** | **9** | **14** | **4[illegible]** 13 |

ዓላማ ተኮር ንሞና

ስዕል 1 የጥናቱአካላይናናሙናየተወሰደባቸውወረዳዎች፣የተሳታፊዎችብዛትእናአመራረጥ

**ለ) ቃለ-መጠይቅ**

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ደግሞ ባህላዊ አልባሳቱ ናጌጣጌጦቹ በማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ቦታ፤ማህበራዊ ፋይዳቸውን፤ በማህበረሰቡ ውስጥ የቁሶቹን ውክልና ወይም ተምሳሌትነትን በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል:: እነዚህን ርዕስ ጉዳዮች በሚመለከት ዝግ እና ልቅ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች ለተሳታፊዎች ቀርበዋል። በዚህ ዘዴ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጧቸው መረጃዎች በማስታዎሻዎች ተይዘዋል።

### ሐ) የቡድንተኮርውይይቶች

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ-መጠይቅ ያልተደረጉ ተሳታፊዎችን በጾታቸው በቡድን በቡድን በማድረግ ግልፅ ባልሆኑ እና ልዩነት ባላቸው አልባሳትና ጌጣጌጥ ውክልና ዙሪያ ውይይቶች እንዲያካሄዱ ተደርጓል:: በእያንዳንዱ ቡድን ከአራት እስከ አምስት አባላት ያለው አምስት የቡድን ተኮር ውይይቶች ተከናውነዋል። ለተወያዩች ውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን በአጥኝዋ እየተነሱ ውይይት ተደርጎባቸዋል።

### *2.5. የጥናቱ መረጃ አተናተንና አቀራረብዘዴዎች*

በጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች ገላጭ(Descriptive) እና ተርጓሚ (Interpretative) ዘዴን በመከተል ተተንትነዋል። የአልባሳቱን እና የጌጣጌጡን አካላዊ ገጽታ ማብራሪያ ከተደረገ በኋላትርጉም ሊሰጡ እንዲችሉ ሁኗል። በመጨረሻም አልባሳቱ እና ጌጣጌጡከሚውሉበት ወይም ከሚጌጡበት የሰውነት ክፍል አንፃር ተከፋፍለው እና ከጥናቱ ዓላማዎች አኳያ በመከፋፈል የጥናቱ ውጤቶች ቀርበዋል።

### *2.6. የሥነ-ምግባር መሮሆዎች አጠባበቅ*

በዚህ ጥናት መሰረታዊ የምርምር ሥነ ምግባር መርሆዎችን ለመጠበቅ ሲባል መረጃ በመስጠት ለተሳተፉ ናሙናዎች  የጥናቱን አላማ እንዲረዱት ገለጻ ተደርጎላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ለብሰው ፎቶ ግራፍ የተነሱ ተሳታፊዎቸ ፎቶ ግራፋቸው በምርምሩ ሪፖርት ወይም ዘገባ ቢካተት እንደማይቃወሙ በቃላቸው አረጋግጥዋል[3]።

## 3. የጥናቱ ውጤትና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል መረጃ የተሰበሰበባቸው አልባሳትእና ጌጣጌጥ አካላዊ ገፅታና ማህበራዊ ፋይዳተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡም ከሰውነት ክፍል መሸፈኛነታቸው እና ከማስዋቢያነታቸው ባለፈ የሚሰጡት ማህበራዊ ፋይዳ ከተለያዩ አጥኝዎች ግኝት አንፃር እየተብራሩ ቀርበዋል፡፡

### *3.1. ባህላዊ አልባሳት*

በዚህ ንዑስ ክፍል ሴቶች የሚለብሱት እንክርት፣ ሙሉ ሽንሽን፣ ጉርድ ሽንሽን እና አርባ ሽንሽን (ቀሚስ) እንዲሁም ወንዶች የሚለብሱት ፎጣ፣ የጉልበት ሱሪ፣ መብሩቅ(ወንጨሬ) እና ጋቢ ከአካላዊ ገፅታቸው አንጻር በገለጻ መልክ ቀርበዋል።

**እንክርት፦**በምልከታው ወቅት እንደተስተዋለው በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ በአብዛኛው የሚለበሰው እንክርት (ስዕል 2 እና 3) የሚዘጋጀው ከተፈተለ ጥጥና ደማቅ ቀለም ካለው ጥለት/ክር/ ነው፡፡እንክርት ከአንገት አንስቶ እስከ ባዕት ድረስ የሴትን ልጅ ውጫዊ የአካል ክፍሎች የሚሸፍን የልብስ ዓይነት ነው፡፡ ከጥጥየሚሰራውእንክርትሁለትዓይነት ገጽታ ሲኖረውየመጀመሪያው አይነት (ስዕል 2)ከታች ጫፉ ላይ ሙሉ በሙሉ ዙሪያውን በጥለት ያጌጠ ሲሆን ሁለተኛው (ስዕል 3) ደግሞ ጥለቱ ከታች ሆኖ ነገር ግን በፊት በኩል ምንም ዓይነት ጥለት ሳይኖረው ከኋላው ብቻ የሚደረግበት የእንክርት ልብስ አይነት ነው፡፡

---

[3]ተጨማሪ የፎቶ ግራፍ መረጃዎችን በማቅረብና በመስጠት እንዲሁም ፎቶ ግራፎቹ በጥናታዊ ፅሑፉ ላይ እንዲሰፍሩ ስለፈቀዱልኝ የምስራቅ ጎጃም ዞን ባህልና ቱሪዝም መመሪያ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በእንክርቱ ጫፍ ላይ ያለው ጥለት ቀለም በለባሾቹ ምርጫየሚወሰን ነው፡፡ለምን ደማቅ ቀለም ያለው ጥለት እንደሚመርጡ የጥናቱ ተሳታፊ በቃለ ምልልስ ሲናገሩ"ደማሴውን [ቀዩን] እና ጌሾ [አረንጓዴ] ዓይነቱን ጥለት የምንወደው አንድያ ሺጋና ደስ የሚል ስለሆነ ነው ሁለትያ ቆሊያችን [መንፈሳችን] ስለወደደውነው"ሲሉ ገልፀውታል (ወ/ሮ ሙሉነሽ፣ ጭምት፣ ቃለ-መጠይቅ፣ መስከረም 10/2008 ዓ.ም)።ይህን ሀሳብም ከቡድንተኮር 1ውይይትየተገኘው ውጤት የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የእንክርቱ ለባሽ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ አቅም ካላት ፊት ለፊቱ በተለያዩ ቀለማትባሸበረቁ ክሮች አስጠልፋ (ጥልፋት) ልትለብሰው ትችላለች።እንክርቱ በሚሰራበት ወቅት እንደለባሾቹ የእድሜ ደረጃ ከስሩ ከጥጥ የተሰራ ወይም ከቦብሊን[4] የተሰራ ጨርቅ ይደረብበታል።ይህምእንክርቱንከተለያዩቆሻሻዎች ለመከላከል እና የለባሿን የሰውነት ክፍል ከውጭ እይታ ለመከላከል እንደሆነ በቡድን ውይይቱተገልጿል። (ቡድን 2፣ ግራራም፣ መስከረም 27/2008ዓ.ም)፡፡ ይህን ሀሳብም ወ/ሮ ዝግጁእና ሌሎች በቃለ መጠይቁ አጠናክረውታል፡፡

እንክርቱን የሚለብሱ ሴቶች በአብዛኛው ከ50 ዓመት በታች የሆኑ ሲሆንያገባች ሴት ከሆነች ከእንክርቱ ጋር ተመሳሳይ ጥለት ያለው ነጠላ ኩታ ከላይ እንደምትደርብበት፤ በወገቧ በደማቅ ቀለማት ያሸበረቀ መቀነት እንደምትታጠቅ እናበእራስ ቅሏ ላይ ነጭ ወይም ጥቁር ቀለም ያለው ሻሽ እንደምታስር በቡድንውይይት ወቅት ተብራርቷል።የእንክርቱ ለባሽባል ያላገባች ከሆነ ግን ምንም ዓይነት መቀነት ወይም ነጠላ አይደረብበትም። (ቡድን 3፣ አባሊባኖስ፣ ታህሳስ 3/ 2008 ዓ.ም)፡፡ ይህ ሀሳብም በምልከታው ወቅት አረጋግጫለሁ፡፡



ሰዕል 2 ጥለት ያለው እንክርት የለበሰች ሴት



ሰዕል 3 ከፊት ጥለት የሌለው እንክርትየለበሰች ሴት

[4]ቦብሊን በፋብሪካ የተሰራ አቡጀዲ መሰል ብትን ጨርቅ ነው።


**ሙሉ ሸንሸን፦**ይህ የልብስ አይነት(ስዕል 4) ከጥጥ የሚሰራ ሲሆንልክ እንደ እንክርት ከአንገት ጀምሮ እስከ ባት ያለውን የሴቶች የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ነው፡፡ይህ ልብስ ከላይ እስከ ታች ሙሉ በሙሉ ተሸብሸቦ ከወገቡ ላይ በላስቲክ የተሰፋ እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡ ልብሱ ሙሉ ሸንሸን የሚለውን ስያሜ ከዚህ እንዳገኘው በቃለ ምልልሱ ሸማ ሰሪው አቶ አሻግሬ (ወጀል፣ ጥቅምት 15/2008 ከታችኛው የልብሱ ጫፍ በኋላ በኩል በአብዛኛው ቀይ ጥለት ይደረግበታል፡፡ይህን ልብስ የሚለብሱት በእድሜያቸው የገፋና መውለድ ያቆሙ ሴቶች እንደሆኑ በቡድን ውይይቱ ተብራርቷል (ቡድን 1፣ ቢቾና ደብር፣ የካቲት 13/2008 ዓ.ም)።

ሙሉ ሸንሸኑን በሚለብሱበት ሰዓት የልብሱን ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ቀለም ያለው ጥለት ነጠላ ኩታ ከላይ ይደርቡበታል፡፡ የመፍተል አቅምካላቸው እራሳቸው ከፈተሉት ጥጥ የተሰራ መቀነት አቅም ከሌላቸው ደግሞ ተመሳሳይ መቀነት ከገበያ በመግዛት ይታጠቁበታል፡፡

ሙሉ ሸንሸን የሚለበሰው በአብዛኛው በአመት በዓል ሲሆን የሚለብሱትም ቤተሰቡንና ከብቶችን ከክፉ መንፈስ ለመጠበቅ እንደሆነ ወ/ሮ ማናየሽ (ወጀል፣ ጥቅምት 15/2008 ዓ.ም) "በአመት ቫል ይህን የምናጠልቀው አመት ቫሉን ለመቋደስ [እና] ቡዙ ዛር እቤት [ይመጣል በሚል ነው]። … ያን ግዜ በጨርቃችን ካልተደሰተ ወይ ሰው ወይ ከብት ይወጋል" ሲሉ ገልጸዋል። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድበበዓል ቀንብዙ በዓይን የማይታይ መንፈስ እቤት ይመጣል ተብሎ ስለሚታመን በአለባበሳችን እና በአመጋገባችን ካልተደሰተ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ እንደሚፈራም በቡድን ተኮር ውይይቱ ተገልጿል።



ስዕል 4 ሙሉ ሸንሸን የለበሰች ሴት




ስዕል 5 ምሪና አምባር የታጠቀች ልጃገረድ

**ጉርድ ሸንሸን፦**ይህ የልብስ አይነት ከጥጥ እና ደማቅ ቀለም ካለው ጥለት/ክር የሚሰራ ሲሆን ልክ እንደ ሙሉ ሸንሸን ከአንገት ጀምሮ እስከ ቁርጭምጭሚት ድረስ የሴትን ልጅ የአካል ክፍል የሚሸፍንነው።በምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት ይህልብስ ከላይ ሰፊና ልቅ ይሆንና ከታች ተሸብሽቦ ወገቡ ላይ በላስቲክ ተይዟል፡፡ይህን የለበሱት በአብዛኛው በእድሚያቸው የገፉና መውለድ ያቆሙ ሴቶች

ናቸው፡፡ ልብሱን በለበሱበት ሰዓት የጉርድ ሽንሽኑን ዓይነት ወይም ተቀራራቢ ቀለም ያለው ጥለት ነጠላ ኩታ ከላይ ደርበውበታል። በተመሳሳይ ቀለም ያሸበረቀ መቀነት ታጥቀውበታል።

ጉርድ ሽንሽን የሚለብሱትበአብዛኛው በአመት በዓል ወቅት ሲሆን የሚለብሱበትምክንያትምልክ እንደ ሙሉ ሽንሽን ሁሉ ቤተሰቡንና ከብቶችን ከክፉ መንፈስ ለመጠበቅ እንደሆነ የቡድን አንዳንድ ተሳታፊዎች ገልጸውልኛል (ቡድን 1፣ ደባ፣ ህዳር 12/2008 ዓ.ም)።ከዚህ ጋር በተያያዘ "...ደማቅ ከረን [ቀለም] ያለው ጥለት የሚወደደው ክፉ ቆሌ [መንፈስ] አይኑ" እንዲያርፍ እንደሆነ በቃለ ምልልሱ ወቅት ወ/ሮ ዝግጁ የተባሉ ተሣታፊ ገልጸውልኛል (የርሞት፣ ህዳር 21/2008 ዓ.ም)።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አልባሳትና ጌጣጌጥ በእነዚህ ሁነቶች የሚለበሱት በለባሾቹ ዘንድ ገና አላለቁም ወይም አላረጁም ተብለው እስከሚታሰቡበት ወቅት ነው፡፡ አልቀዋል ተብለው ከታሰቡ በኋላ ለገበያ ወይም ለአዘቦት[5] ልብስ በመሆን እንደሚያገለግሉ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ አረጋግጫለሁ፡፡

***አርባ ሽንሽን (ቀሚስ)፡-*** ይህ ልብስ (ስዕል 5 እና 6) ከላይ እንደተዘረዘሩት አልባሳት በተጠኝው ማህበረሰብ የሚሰራ ሳይሆን ብትን ጨርቂ ከገበያ ተገዝቶ በአካባቢው ባሉ ልብስ ሰፊዎች የሚሰፋእንደሆነ በቡድን ውይይቱ ወቅት ተጠቅሷል፡፡ በምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት ከአንገት ጀምሮ እስከ ጉልበት ወይም ከባት ወረድ ብሎ ያለውን የሰውነት ክፍል ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እስከ ጉልበት የሚለብሱት በቆላማው የአየር ንብረት አካባቢ ያሉ ሴቶች ሲሆኑ ከባት ወረድ ብሎ የሚለብሱ ደግሞ በደጋማው አካባቢ ያሉ ሴቶች ናቸው፡፡

አርባ ሽንሽን ከአንገትእስከታችኛው የጡት ክፍል ድረስ በተለያየ የቁልፍ 'ዲዛይን'ሊያሸበርቅ ይችላል፡፡ በልብሱ ላይ ቁልፍ የሚደረድሩት በአብዛኛው ያላገቡ ወይም አግብተው የፈቱ ሴቶች ሲሆኑ ያገቡና የወለዱ ሴቶች ግን አይጠቀሙበትም፡፡ ለምን እነዚህ ብቻ እንደሚጠቀሙበትም የጥናቱ ተሳታፊ በቃለ ምልልሱ እንዲህ ስትል ገልጻልኛለች።

> "በጨርቁ ላይ [ለአቅመ ሄዋን] የደረሰች ወይም ሁለት ሶስቴ ወግ አይታ [ትዳር ይዛ] የፈታች ብቻ ናት የምትደረድረው፡፡ ያገባች ተሆነች በባሏ ላይ ምን አስባ ነው ተብላ ትነወራለች፡፡... ትዳር የሌላት ተሆነች ግን የቁንጅና መገለጫ ጭምር ስለሆነ ትዳር መፈለጓን ያመላክታል፡፡"(ወ/ሮ ንፁህ፣ የጣይቷ፣ ኅዳር 27/2008 ዓ.ም) ይህንን ሀሳብም የቡድን 5 ተሳታፊዎች አጠናክረውታል፡፡

በምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት አርባ ሽንሽን የምትለብሰ ሴት ያገባች ከሆነ ወገቧ ላይ መቀነት (ስዕል 6)ትታጠቃለች፡፡ በራሷ ላይ ሙሉ በሙሉ ጥቁር ቀለም ያለው አስር ሜትር የሚደርስ ጥቁር የራስ ማሰሪያ (ባውንድ ስዕል 6) ወይም በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀ ሻሽ ታስራለች፡፡ በሁለቱም እጇ ላይ አንባር ታደርጋለች። በአንገቷ ላይ የተለያዩ ጌጣጌጦችን (ለምሳሌ ጨረቃ ጠልሰም) ታደርጋለች። ብዙ ጊዜ የሚለበሰውም አዲስ ከሆነ አመት በዓል ቦታና በገበያ ቦታ ሲሆን የተወሰነ ማርጀት ከጀመረ በስራ ቦታ ይለበሳል፡፡


ያላገባች ከሆነች እና ለአቅመ አዳም የደረሰች ከሆነች ደግሞ ይህንን ልብስ በምትለብስበት ሰዓት ከቆዳ በቀጭኑ እንደ ቀበቶ የተዘጋጀ ምሪ (አረብ) (ስዕል 5) በወገቧ ታስራለች። ይህን ምሪ በወገቧ የምታስረውም ለአቅመ አዳም የደረሰች ልጃገረድ መሆኗንና የእሷን አዳም ካገኘችለማግባት የተዘጋጀች መሆኗን መግለጫ ነውሲሉ የቡድን ሶስት ተወያዮች አብራርተዋል (ቡድን 3፣ አባሊባኖስ፣ ታህሳስ 3/ 2008

---

[5] በአዘቦት ማለት ሁልጊዜ የሚለውን ቃል ይተካል፡፡

ዓ.ም)። ይህን ሀሳብም ያሳብእና ሌሎች በቃለ መጠይቁ አጠናክረውታል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ምሪ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለማግባትን እንዲሁም ለአቅመሂዋን መድረስን መግለጫ መሆኑን ነው።

**ጋቢ፦** ጋቢ (ስዕል 7 እና 8) ማለት ከጥጥ የሚሰራ ሲሆን የማህበረሰቡ አባላት የሆኑት ሽማግሌዎች በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ማለትም እርቅ ቦታ፣ ሰርግ ቦታ፣ ቤተእምነት እና ሃዘን ቦታ ሲሄዱ የሚለብሱት ነው። ለምን ይህ ልብስ በእነዚህ አውዶች እንደሚለበስ አቶ በላይ በቃለ ምልልሱ እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል። "በደንባችን በደስታም ሆነ በመከራ ቦታላይሲሄድ አንድ ሽማግሌ ጋቢ ካለበሰ ወይ ሽማግሌ አይል የምን መቅለል ነው ይባላል። ወይ ደግሞ የሰውን ደስታና መከራምን ቢንቅ ነው ተብሎ ይነወራል" (አቶ በላይ፣ እንደሽኝት፣ ጥር 14/2008 ዓ.ም)።በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ነጭ ልብስ የለባሹንም ሆነ የተገኘበትን አውድ ክብር መግለጫ ተደርጎ ይወሰዳል።




ስዕል 6 በባውንድ፣ በመቀነት፣ በጨረቃ ጠልሰምና በአምባር ያጌጠች እና አርባ ሽንሽን የለበሰች ሴት


**መብሩቅ (ወንጨሬ)፦** መብሩቅ የተባለው የልብስ አይነት (ስዕል 7) ከወገብ በታች የሚለበስ ሲሆን የሚዘጋጀው በፋብሪካ ተሰርቶ ከሱቅ ከሚገዛ ብትን ጨርቅ ነው። ብትን ጨርቁን ልብስ ሰፊዎች ዘንድ ይዞ በመሄድ በለባሹ ልኬት መሰረት ይሰፋል። በምልከታዩ እንዳስተዋልሁት መብሩቅ ከወገብ በታች እስከ ጉልበት ደረስ ሰፊ ሲሆን ከጉልበት ጀምሮ እስከ ቁርጭምጭሚት ያለው ደግሞ በእግር ውፍረት ልክ ተጣብቆ የሚዘጋጅ ነው።

መብሩቅ የሚለበሰው አዛውንት ሽማግሌዎች ወደ እርቅ፣ ቤተ እመነት፣ እና ማህበር ሲሄድ ነው። በቡድን ውይይቱ እንደተብራራው አንድ ሰው መብሩቅ ለብሶ ከታየ በአካባቢው ሽማግሌ እና የተከበር ሰው መሆኑን ያመላክታል (ቡድን 5፣ የቀጋን የካቲት 14/2008 ዓ.ም)። ስለሆነም ወንጨሬ የማህበራዊ ክብር እና የእድሜ መገለጫ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

*የጉልበት ሱሪ፦* የጉልበት ሱሪ (ስዕል 8) ልክ እንደመብሩቅ ሁሉ ከወገብ በታች የሚለበስ፣ ከሱቅ በሚገዛ ብትን ጨርቅ የሚዘጋጅ እና ማህበራዊ ከበሬታን ለማግኘት በአዛውንት ሽማግሌዎች የሚለበስ ሲሆን አሰራሩ ከመብሩቅ በተወሰነ መንገድ ይለያል። የጉልበት ሱሪ ከወገብ ጀምሮ  እስከ ጉልበት ያለው ሰፊ ሲሆን ከጉልበት ጀምሮ እስከ ባት ያለው ስፋት በለባሹ ባት ውፍረት ልክ  የሚዘጋጀ የልብስ አይነት እንደሆነ በምልከታየ ማረጋገጥ ችያለሁ። ለባሾችም በቃለ መጠይቁ ገልፀውልኛል፡፡




ስዕል 7 ጋቢ እና ወንጨሬ (መብሩቅ) የለበሰ ሰው




ስዕል 8 የጉልበት ሱሪና ጋቢ የለበሰ ሰው

**ፎጣ፡**ብምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት ፎጣ ማለት ከክር የሚሰራ ሽማግሌዎች ወይም ሙሽሮች ራሳቸው ላይ የሚያደርጉት የልብስ ዓይነት ነው።ሙሽራና ሽማግሌ እራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት የክብር መገለጫ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊ በቃለ ምልልሱ ገልፀውልኛል (አቶ ሞገስ፣ ደባ፣ ጥር 12/2008 ዓ.ም)።

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ ወንድ ሙሽራ እራሱ ላይ ከሚጠመጥመው ፎጣ በተጨማሪ ለአርባ ቀን ያህል በእጁ የብረት ከዘራ ይይዛል።ይህን የብረት ከዘራ በእጃቸው የሚይዙት ብረቱ ሙሽራውን ከክፉ መንፈስ ይጠብቀዋል ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ አቶ አባተ(ስናን፣የካቲት 15/2008 ዓ.ም)እና አቶ ይበልጣል(ቁይ፣የካቲት 14/2008 ዓ.ም)የተባሉ ቃለ መጠይቅ ተደራጊ ገልጸዋል።

ይህን የፎጣ ጥምጣም ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት በደጋማ የአየር ንብረት አካባቢ(ለምሳሌ፦ ስናን ወረዳ) የሚኖሩ ሽማግሌዎች እና ሙሽሮች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ይህ በራስ ላይ የሚጠመጠም ፎጣ የሰዎችን የህይወት ምዕራፍ እና የለባሾችን ከወዴትነት መግለጫ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

*3.2. ባህላዊጌጣጌጦች*

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ በርከት ያሉ ጌጣጌጦች (በተለይ የሴቶች) አሉ፡፡እነዚህ ጌጦች እንደየአገልግሎታቸው የተለያዩ ሲሆኑ በዚህ ንዑስ ክፍል የሚተነተኑት ጌጣጌጦችም ትዕምርታዊ ፋይዳቸው የጎሉትን ብቻ በመውሰድ ነው:: እነዚህ ጌጦችም እንደሚደረጉበት የአካል ክፍል የራስ፣ የአንገት፣ የእጅ እና የእግር ጌጣጌጦች በማለት ተተንትነዋል።

**3.2.1.የራስጌጦች**

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ በራስቅል ላይ የሚደረጉ የተለያዩ ጌጦች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ባውንድ[6] ተጠቃሽነው።

***ባውንድ፦***በምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት ባውንድ (ስዕል 6) ከብትን ጨርቅ የሚዘጋጅናያገቡ ሴቶች በራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ነው። አንድ ሴት በራሷ ላይ የምትጠመጥመው ባውንድ ርዝመቱ ከአራት እስከ አስር ሜትር ሊደርስ ይችላል።የሜትሩን ብዛትየሚወስነው የጠምጣሚዋ የኢኮኖሚ አቅም ነው። ጠምጣሚዋ የተሻለ ኢኮኖሚ ካለው ቤተሰብ የተወለደች ወይም የተጋባች ከሆነች በርከት ያለ ሜትር ያለው ባውንድ ታስራለች።በተለይ አግብታ የፈታችና ሌላ ባል ለማግባት የተዘጋጀች ሴት ከሆነች በርከት ያለ ሜትር ያለው ጥቁር ባውንድ በማሰር ሌላ ባል ለማግባት ዝግጁ መሆኗን ለማህበረሰቡ ታውጅበታለች ሲሉ ገልፀዋል። (ቡድን 4፣ ጭምት፣ ጥር 7/2008 ዓ.ም)

በሌላ በኩል *መጀመሪያቸውን ያላገቡ* ሴቶች ግን ምንም አይነት ባውንድ የማይጠመጥሙ ሲሆን አግብተው በትዳር የሚኖሩና ልጅ የወለዱት ግን ርዝመቱ አጠር ያለ ከአራት እስከ አምስት ሜትር ብቻ ሊጠመጥሙ ይችላሉ። ምክንያቱም በትዳር ያሉና ልጅ የወለዱ ሴቶች ከአምስት ሜትር በላይ ቢጠመጥሙ በትዳራቸው ላይ መደረብ ፈልገዋል ተብሎ በማህበረሰቡ ስለሚተቹና በቤቱ አባወራ ላይ የቅናት መንፈስ ያሳድራል ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊ በቃለ-መጠይቁ ወቅት ጠቁመዋል።(አቶ አምባቸው፣ ታህሳስ 25/2008 ዓ.ም) እንዲሁም በቡድን 4 ተሳታፊዎች ሀሳቡ ተደግፏል፡፡

በመሆኑምበተጠኘው ማህበረሰብብዙ ሜትር ያለው ባውንድ መጠምጠም ጋለሞታ(አግብታ የፈታችና ለማግባት የተዘጋጀች) መሆኗንየሚገልፅሲሆንትንሽ ሜትር የጠመጠመችደግሞበትዳር የምትኖርና የወለደች መሆኗን ሲገልፅ፤ ምንም ባውንድ አለመጠምጠም ደግሞ ገና ምሪ ያልፈታች (ለመጀመሪያ ጊዜ ያላገባች) ለወደፊት ግን ማግባት የምትችል መሆኗን ከላይ ከቀረበው ትንታኔ መረዳት ይቻላል።

**3.2.2.የአንገትጌጦች**

በምልከታው ወቅት እንዳስተዋልሁት በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የሚደረጉ የአንገት ጌጦች (ከስዕል 9 እስከ 11) በአብዛኛው ከብር የሚሰሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ከዶቃ (ጨሌነገሮች) የሚሰሩሊሆኑ ይችላሉ። እንደየተሰሩበት እቃ የተለያየክብር ወይም ግምት ጌጦችን ላደረጉ ሴቶች ይሰጣቸዋል፡፡የአንገትጌጦች ብዙዎቹ ከእናትወደ ልጅ ተላልፈው ወይም በስጦታ መልክከ ትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉ እንደሆኑ ወይዘሮ ያሳብናወይዘሮ ታዳምቅ (የቦ፣ ታህሳስ 23/2008 ዓ.ም) ገልፀዋል። ከእነዚህ የአንገት ጌጦች መካከልም ዋና ዋናዎቹ መንታ ድሪ፣ ድርብ ሽርብና ጥምዝ ድሪ ይገኙበታል።

---

[6]ባውንድ ምንምእንኳንየልብስ ዘር ቢሆንምበሴቶች ራስ ላይ ለጌጥ አገልግሎትስለሚውል ለትንተናእንዲመችበማሰብበጌጣጌጦችምድብውስጥተካቷል፡፡

**መንታ ድሪ፡-** ይህየአንገትጌጥ(ስዕል 9) በአብዛኛውሙሉ በሙሉ ከብር የሚሰራ ሲሆንበአንድ ጊዜ በአንገት ላይ የሚደረገው እስከ ስድስት እጥፍ ወይም ዙር እንደሚደርስ ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ መንታ ድሪ ላይ 'ጎለጎታ' የሚባል አራት መዓዘን የሆነ የድሪውን ጫፎች የሚያገናኝ ማጫወቻ አለው።

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ መንታ ድሪ ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው የአንገት ጌጥ አይነቶች አንዱ ነው፡፡በመሆኑም ይህ የአንገት ጌጥ ውድ ከሚባሉት ውስጥ እንደሚመደብ በቃለ ምልልሱ ተጠቁሟል (ሙሉጌታ፣ ሊቀበሃና፣ ታህሳስ 13/2008 ዓ.ም)። ይህን የአንገት ጌጥ የሚያደርጉት ብዙ ጊዜ በእድሜ የገፉ ባለፀጋ እማወራዎች የአባት አምላክ ያለባቸው እናቶች በበዓላት ቀናት እና አራስ ሴቶች ናቸው፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡

> የአባት አቴቴ [አምላክ] ኑሮባቸው በባላት ቀን የብር መንታ ድሪ ካላደረጉ ያባት አቴቴው [አምላኩ] ተቆጥቶ ልጆች ወይም ከብቱ ላይ ጉዳት ያደርሳል እንላለን፡፡ ከበርቲዎች ደ'ሞ መንታ ድሪ ካልገዙና ካላደረጉ [በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ] ገብጋባ [ስግብግብ]ይባላሉ፡፡ … አራሷም መንታ ድሪ የምታረገው የማሪያም አራስ ስትሆን ከርኩስ መንፈስ ስለሚጠብቃት ነው።

(ወ/ሮ ስለናት፣ ዝግባ፣ የካቲት 03/2008 ዓ.ም)፡፡

መንታ ድሪ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ከጌጥነት ባለፈ የሃብት መገለጫ፣ የቤቱን የአባት አምላክ ማስደሰቻ እና ከክፉ መንፈስ መጠበቂያ ተደርጎ እንደሚታሰብ መረዳት ይቻላል።



ስዕል 9 መንታ ድሪ



ስዕል 10 ድርብ ሽርብ ድሪ

**ድርብ ሽርብ ድሪ፡-** ድርብ ሽርብ ድሪ (ስዕል 10)የአንገት ጌጥ የሚሰራው ከብርና ከክር ሲሆን ይህየአንገትጌጥከመንታ ድሪ ቀጥሎ ተፈላጊና ውድ ጌጥ እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀውልኛል፡፡ ከዚህ ድሪ ጋር የሚሸረበው ክር ብዙ ጊዜ ወይን ጠጅ ቀለም ያለው እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡ ወይን ጠጅ ቀለም ያለው ክር በማህበረሰቡ ዘንድ ለጌጥነት እንደሚመረጠየቡድን ተወያዮች ገልጸዋል (ቡድን 2፣ ግራራም፣ መስከረም 10/2008 ዓ.ም)።

ድርብ ሽርብ ድሪ በአንገታቸው ለጌጥነት የሚጠቀሙት ሙሽራ የሆኑት ሴቶች በሙሽርነታቸው ወቅት እና አራስ ሴት የወለደችውን ወይም የወለደቻትን ልጅ ክርስትና እስከምታስነሳ ድረስ ነው፡፡ ሙሽሪትም ሆነች አራሷ ለራሳቸውይህ ጌጥ ባይኖራቸው ከሌላ ሰው ተውሰውያደርጉታል ምክንያቱም የክብር መገለጫና ሙሽሪትን በሙሽርነቷ ወቅት አራሷንም እንዲሁ በአራስነቷ እሷንና ህፃኗን/ኑን ከሚተናኮል ክፉ

መንፈስ ይከላከልላቸዋል ተብሎ እንደሚታመን በቃለ ምልልሱ ወቅት ተገልጿል (ወ/ሮ ወሰኔ፣ ደሳ፣ ታህሳስ 21/2008 ዓ.ም)። የቡድን 3 ተወያዮችም ሀሳቡን አጠናክረውታል፡፡

በመሆኑምድርብ ሽርብ ድሪ ውበትን ከማገናፀፉ በተጨማሪ የማህበረሰቡን የህይወት ምዕራፍ ሽግግር አመልካች ሊሆን ይችላል::

**ጥምዝ ድሪ:-**ይህየአንገትጌጥ (ስዕል 11) ከብርና ከቆርቆሮ የሚሰራ ሲሆንነጠላውድሪ ከክር ጋር ተጠምዞ የሚደረግነው:: በተጠመዘዘው ክርና ድሪ ላይ ከመዳብ የተሰራ ቀለበት እንደሚደረግበት አስተውያለሁ፡፡ ይህንጌጥየምታደርገው ሙሽሪት በሙሽርናዋ ወቅት ሲሆን የተደረገው ከቆርቆሮ የተሰራ ከሆነ ለጌጥነት መሆኑን የሚያመላክት እንደሆነናከብር የተሰራ ከሆነ ደግሞ ከጌጥነት ባለፈ ብርና መዳብ ከክፉ መንፈስ ይጠብቃሉ ተብሎ እንደሚታመን በቡድን ውይይቱ ተገልጿል(ቡድን 1፣ ቢቾና ደብር፣ የካቲት 13/2008 ዓ.ም)። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ብርና መዳብ ከክፉ መንፈስ ይጠብቃል ተብሎ እንደሚታመን መረዳት ይቻላል፡፡

### 3.2.3.የእጅጌጥ

የእጅ ጌጣ ጌጥ የሚባሉት የማህበረሰቡ አባላት በክንዱና በእጣቱ ላይ ለመዋቢያነት የሚያደርጓቸው ሲሆኑ በዚህ ጥናትም በማህበረሰቡ ዘንድ ትዕምርታዊ ፋይዳው ጎልቶ የሚታየው አንባር የእጅ ጌጥ ላይ ትንታኔ ተደርጎበታል፡፡

**አምባር፡-** ይህ የእጅ ጌጥ (ስዕል 5 እና 6) ከብር የሚሰራና ክንድ ላይ የሚደረግ ሲሆን ሙሽራ፣ ባለሃብት እናባለአባት አምላክ[7]ወይም ባለአቴቴ ሴቶች የሚያደርጉት ነው፡፡ እነዚህ ሴቶች ብቻ የሚያደርጉበትን ምክንያት ወ/ሮ ቦሴ (ቀቢ፣ ጥር 03/2008 ዓ.ም) እንዲህ ገልፀውታል።


> ብር አምባር ለጌጥ ነው እሚደረግ። ... [ብር አምባር] የሚያረጉ ሙሽሮች ጭምር ናቸው። ሙሽራይትን [በሙሽርነቷ ወቅት] ከሚተናኮላት ምናምን [ክፉ መንፈስ]እንዲጠብቃት ነው። ... [ብር አምባር] በሰኔና በመስከረም የሚያደርጉት ደግሞ አቴቴው እንዳይቆጣት ሊደረግ ይችላል። ከበርቲ ተኮነ ደ'ሞ ሃብታቸውን ማሳያ ብር አምባር ሊያረጉ ይችላሉ።ወ/ሮ ቦሴ (ቀቢ፣ ጥር 03/2008 ዓ.ም)

በአጠቃላይ ይህ የእጅ ጌጥ ከጌጥነቱ ባለፈ የተገልጋዩን ማንነት ምንነት ሊያሳይ ይችላል።

### 3.2.4.የእግርጌጥ

**አልቦ፡-**ይህየጌጥአይነት(ስዕል 12) እግር ላይ የሚደረግ ሲሆን ሙሽሮች እንዳ አላቸው የኢኮኖሚ አቅምከብር ወይም ከቆርቆሮ የተሰራ አልቦያደርጋሉ፡፡አልቦጥቃቅን ክብ ብሮችን ወይም ቆርቆሮዎችን በጠንካራ ክር በማያያዝ የሚሰራ እንደሆነ አስተውያለሁ፡፡ ሴት ሙሽሮች ውበታቸውን ለማጉላት እንደሚጠቀሙበትየቡድን ተወያዩች ገልጸዋል (ቡድን 3፣ አባሊባኖስ፣ ታህሳስ 3/2008 ዓ.ም)። ከዚህ በተጨማሪየአባት አምላክ (አቴቴ) ያለባቸው ሴቶች ደግሞ አባት አምላካቸውን ያስደስተዋል ብለው ስለሚያምኑ በባዓላት ቀን ያጌጡበታል ሲሉ በቃለ ምልልሱ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀውልኛል (ደጊቱ፣ አምቡሳም፣ ጥር 30/2008 ዓ.ም)፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ አልቦ የህይወት ምዕራፍ ሽግግርን ማሳያና ከክፉ መንፈስ መከላከያ ተደርጎ እንደሚታመን መረዳት ይቻላል።

[7] ባላባት አምላክ ማለት ከቀደምት ወላጆቻቸው ተወራርሶ የመጣ ቤተ-ሰቡን ከመጥፎ ነገር የሚጠብቅ መንፈስ ማለት ሊሆን ይችላል።



ስዕል 11ጥምዝ ድሪ



ስዕል 12አልቦ

*3.3.የባህላዊአልባሳትእናጌጣጌጥማህበራዊፋይዳ*

በዚህ ክፍል ከላይ የተተነተኑ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ያሏቸው ትዕምርታዊ ፋይዳዎች ይዳሰሳሉ፡፡ የአልባሳቱንና ጌጣጌጡን ማህበራዊ ፋይዳዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ከሚያስተላልፉት ማህበራዊ መልዕክት በመነሳት በአራት ዋና ዋና ዘርፎች ጠቅልሎ መመልከት የሚቻል ሲሆን እነዚህም፦ (1) የህይወት ምዕራፍን መግለፅ፣ (2) እድሜን ማመልከት፣ (3) ማህበራዊ የኑሮደረጃንማሳወቅ፣ (4) ክፉመንፈስን መከላከልና (5) ማህበራዊ ሁነቶችን ማሳወቅ ናቸው። እነዚህ ማህበራዊ ፋይዳዎች ከዚህ በፊት ከተጠኑ ጥናቶች ጋር በማቀራኘት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.3.1. የህይወት ምዕራፍን መግለፅ

የተጠኘው ማህበረሰብ አልባሳት እና ጌጣጌጥ የማህበረሰቡን የህይወት ምዕራፍ በጉልህ የሚያሳዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- "ምሪ/አረብ" (ስዕል 5)በመባል የሚታወቀው የወገብ ጌጥ በወገባቸው የሚያስሩ ሴቶች ለአቅመ ሄዋን የደረሱና ባል ለማግባት ዝግጁ የሆኑ ልጃገረዶች ናቸው። ስለዚህ በማህበረሰቡ ምሪ ያሰረች ሴት ባል ካለማግባት ወደ ማግባት የህይወት ምዕራፍ ለመሸጋገር ዝግጁ መሆኗን ሲገልፅ ከተፈታ ደግሞ ካለማግባት ወይም ከኮረዳነት (Puberty) ወደ ትዳር ህይወት መሸጋገሯን ያሳያል፡፡

"አልቦ" በመባል የሚታወቀው የሴቶች የእግር ጌጥ ደግሞ አንዲት ሴት ከብቸኝነት ህይወት ወደ ትዳር ህይወት መሸጋገሯን እና ለእናትነት መብቃቷን ያመላክታል፡፡ በወገባቸው ላይ የሚታጠቁት መቀነት ደግሞ እንደ አስተጣጠቁ የሴቶችን የህይወት ምዕራፍ ይጠቁማል። የታጠቀችውን መቀነት ጎፍላ በፊቷ በኩል ጨርሳ ሳትቋጥር የታጠቀች ሴት አግብታ የፈታችና ሌላ ባል ለማግባት የተዘጋጀች (ጋለሞታ) መሆኗን ሲጠቁም መቀነቱን ጨርሳ የታጠቀች ሴት ደግሞ ያገባችና በትዳር የምትኖር መሆኗን በማህበረሰቡ ዘንድ አመላካች ነው።

ድርብ ሽርብ ድሪና ጥምዝ ድሪ በአንገቷ ላይ ያደረገች ወጣት ሴት ደግሞ ሙሽራ መሆኗንና ወደ አቅመ ትዳር መሸጋገሯን ለማህበረሰቡ ሲጠቁም አግብታ እነዚህን ጌጦች ያደረገች ሴት ደግሞ ወደ እናትነት የሕይወት ምዕራፍ መሸጋገሯን ይጠቁማል።

በተጨማሪምፎጣ እራሱ ላይ ጠምጥሞ የብረት ከዘራ በእጁ የያዘ ወጣት ወንድ ካለማግባት ወደ ማግባት መሸጋገሩን ያመላክታል።

### 3.3.2. እድሜን ማመልከት

ጥናቱ እንዳመለከተው የተጠኘው ማህበረሰብ ባህላዊ አልባሳት እና ጌጣጌጥ የማህበረሰቡን አባላት እድሜ የሚያመላክት ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ Clark (1986) አልባሳት እና ጌጣጌጥ ባላቸው

ትዕምርታዊ ፋይዳ የሚጠቀምባቸውን ግለሰብ የእድሜ መጠን ይገልፃሉ ሲሉ አብራርቶታል፡፡ ለምሳሌ፡- በዚህ ጥናት “ጋቢ” የተባለውን ልብስ የሚለብስ ሽማግሌ ሰው እንደሆነ ተጠኝዎች ገልጸዋል።

ሌሎች እንድሜን አመላካች የሆኑ ልብሶች “እንክርት” (እድሚያቸው ከ50 ዓመት በታቸ የሆኑ የሚለብሱት) እና “ሙሉ ሽንሽን” (በእድሜ የገፉ ሴቶች የሚለብሱት) በመባል የሚታወቁት ናቸው።ለምሳሌ፡- “ሙሉ ሽንሽን” ልብስ እድሜዋ ከ45 በላይ የሆነች ሴት የምትለብሰው ሲሆን ከዚህ በኋላ መውለድ አለመቻሏን (ማረጧን) የሚያሳይ ነው፡፡

እንደአልባሳቱ ሁሉጌጣጌጦችም የእድሜ እርከንን ማመልከት ይችላሉ። ከስምንት እስከ አስር ሜትር የሚደርስ ባውንድ የእራስ ጌጥ የጠመጠመች ሴት የወጣትነት እድሜ አመላካች ነው፡፡ይህን ጌጥ የሚያደርጉ ሴቶች አግብተው የፈቱና ሌላ ለማግባት የሚፈልጉ (ጋለሞታ) ሴቶችን ጠቋሚነቱ በማህበረሰቡ ዘንድ የጎላ ሚና ይጫወታል።

### 3.3.3.ማህበራዊ የኑሮ ደረጃን ማሳየት

የተጠኝው ማህበረሰብ ባህላዊ አልባሳት እና ጌጣጌጥ ማህበራዊ የኑሮ ደረጃን የማሳየት አቅም ሊኖራቸው ይችላል።ይህ ሚናም በተለይ በጌጣጌጦች ላይ የጎላ ነው፡፡ የጌጣጌጦች ብዛትና ጥራት ማህበራዊ የኑሮ ደረጃ (ለምሳሌ፡- በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ልዩነት ማለትም የሃብትና የስልጣን ልዩነቶች) መግለጫ ትዕምርቶች ናቸው።

ማህበራዊ ደረጃን ከሚያሳዩ ጌጣጌጦች መካከል “መንታ ድሪ” እና“አምባር” የእጅ ጌጦች የተወሰኑት ናቸው። እነዚህ ጌጣጌጦች ዋጋቸው ውድ በመሆኑ የሚያጌጡባቸውሰዎች በአካባቢው የባለስልጣን ሚስቶች እንዲሁም በኢኮኖሚ ደረጃቸው ከአካባቢው ሴቶች የተሻሉት እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። ስለሆነም ጌጣጌጡ የማህበረሰቡን ወይም የግለሰቡን ማህበራዊ ደረጃና የኢኮኖሚ አቅም ሊገልፁ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ አፀደ (2003)፣ Clark (1986) ጌጣጌጦች ባላቸው ትዕምርታዊ ፋይዳ የሚጠቀምባቸውን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ማንነት፣ የኑሮደረጃ ይገልፃሉ ሲሉ አብራርተውታል፡፡

### 3.3.4. ክፉ መንፈስን መከላከል

በጥናቱ ተሳታፊ የማህበረሰቡ አባላት መጥፎ ነገሮች እንዳይገጥሟቸውና የወደፊት ኑሯቸው የተስተካከለ እንዲሆን የተለያዩ አልባሳትንና ጌጣጌጦችን በመጠቀም ክፉ ብለው የሚያምኑትን መንፈስ ለመከላከል ይሞክራሉ፡፡ በተመሳሳይ Gracia (2008) አልባሳት በአንዳንድ ማህበረሰቦች ዘንድ ከተለያዩ ክፉ መናፍስት የመከላከል ተግባር እንዳላቸው ገልጿታል፡፡ ለምሳሌ፡- የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች “ሙሉ ሽንሽን”(ሰዕል 4) የተባለው ባለሰፊ ቀይ ጥለት ልብስ የሚለበሰው ለባሿንና የለባሿን ልጆች ከክፉ መንፈስ ይጠብቃል ተብሎ ስለሚታመንነው፡፡

ከአልባሳቱ በተጨማሪም መንታ ድሪ፣ ድርብ ሽርብ፣ ጨረቃ ጠልሰም እና ጥምዝ ድሪ የአንገት ጌጦች፣ አምባር የእጅ ጌጥ እና አልቦ የእግር ጌጥ ከሌሎች ፋይዳዎቹና ትዕምርቶቹ በተጨማሪ የአጊያጯን ቤተሰብና ከብቶችከክፉ መንፈስ ለመከላከል ሲባል ነው፡፡

ስለሆነም በተጠኝው ማህበረሰቡ ዘንድ ነጭና ቀይ ቀለም ያላቸው አልባሳት እና ከብርና መዳብ የተሰሩ ጌጣጌጦች በባህሉ መሰረት ለክፉ መንፈስ መከላከያና ማባሪያም ሁነው የሚገለግሉ መሆኑ ቢያንስ ሥነ-ልቦናዊ ደህንነትንና ማህበራዊ ትስስርን የማጎልበት ፋይዳ ሊኖራቸው እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

### 3.3.5. ማህበራዊ ሁነቶችን መጠቆም

ማህበራዊ ሁነቶች በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ አጋጣሚዎችን ማለትም ሀዘን፣ ሰርግ ልደት እና ክርስትና ሊያጠቃልል ይችላል። ይህ ጥናት በተከናወነባቸው ማህበረሰብ ክፍሎች እነዚህን ማህበራዊ ሁነቶች ለማሳወቅ ባህላዊአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ የራሳቸው የሆነ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይጫወታሉ። በተለይ የባህላዊ አልበሳቱ እና ጌጣጌጡ ቀለም ከፍተኛውን ቦታ ይይዛሉ።

በእነዚህ አካባቢዎች ባህል መሰረት ጥቁር ቀለም የሃዘን መገለጫ ወይም የመጥፎ አጋጣሚ መግለጫ ተደርጎ ስለሚወሰድ ዘመድ ወይም በቅርብ የሚያውቁት ሰው በሞት ሲለያቸው ጥቁር ከለበሱ ሰዎች ሀዘን ላይ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። አንድ ሰው ሲሞትም ጥቁር ቀለም ያለው ነገር ተፈልጎ ለምሳሌ፡- የብረት ምጣድ ጥላሸት ተፈልጎነጭ ልብሶች ይነከራሉ። እነዚህ የተነከሩት ልብሶችም ወደ ጥቁርነት ይቀየራሉ። በዚህ ጥቁር ቀለም በሆነው ልብስ ላይ ሴቶች የሚቹን/ቿን ልብስ በአንገታቸው ይይዛሉ፡፡ ባል የሞተባት ከሆነ የባሏን ሱሪ ዘቅዝቃ በአንገቷ ትይዛለች፣ አባት ወይም ወንድም ከሞተባት ኮት ሸሚዝ በጀርባዋ በኩል ትደርባለች፣ ወጣት ገና ያላገባች ልጅ ከሞተችባት ስታገባ ያጌጠችውን በራስ ማሰሪያዋ ላይ ታደርጋለች። አንዱን ነጠላ ከወገባቸው በታች ይታጠቃሉ።ሴቶች የራስ ፀጉራቸውን ሙሉ በሙሉ ይላጫሉ። በአንገታቸው ላይ እስከ አርባ ቀን ነጭ ክር ያስራሉ፣ በወገባቸው ገመድ ይታጠቃሉ ሌሎች ጌጦችን ያወልቃሉ። ከቀብር ቀን በኋላ የነጠላቸውን ጥለት ወደ ላይ አዙረው ይለብሳሉ።ይህም በህይወታቸው አለኝ የሚሉትን ሰው ማጣታቸውንና በከባድ ሃዘን ውስጥ መሆናቸውን ያመላክታል።

በዚህ ጥናት ተሳታፊዎች ዘንድ ጥቁርቀለም መጥፎ እድል ወይም አጋጣሚተደርጎቢወሰድም አፀደ (2003) በኮንሶ ብሄረሰብ ጥቁርቀለም በጣም ተፈላጊና ገድ ያለው ወይም እድለኛ ተደርጎ እንደሚወሰድ በጥናት ዘገባዋ ገልጻለች። እንደGlacia (2008) አገላለጽ ይህ የሚያመለክተው በአልባሳቱ ትዕምርቶች አማካኝነት የሚተላለፈው መልዕክት ትርጓሜ የሚወሰነው በለባሹ ማንነት፣ በመለበሻ አጋጣሚው እና በመለበሻ ቦታው እንደሆነ ነው።ከዚህ በተጨማሪም በተጠኝውማህበረሰብ ዘንድ የጌጦች መደረግ ብቻ ሳይሆን አለመደረግ ወይም መነሳት፣ የአንድን ልብስ አለባበስ ቀይሮ መልበስም በማህበረሰቡ ዘንድ ተግባቦትን የመፍጠር ትልቅ ማህበራዊ ፋይዳ እንዳለው ያሳያል።

ሌላው የጥናቱ ተሳታፊዎች በባህላዊ አልባሳቱና ጌጠጌጡ ከሚገለፁባቸው ማህበራዊ ሁነቶች ውስጥ የሙሽርነት ጊዜ ነው:: "አልቦ" (ስዕል 12) ተብሎ የሚጠራውን ጌጥ ያደረገች አንድ ወጣት ሴት የቅርብ ሙሽራ እንደሆነች ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ተመልክቶ ሊረዳት ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም "እንሶስላ"የሚባል ቀይ ቀለም ያለው ነገር እግሯን ተቀብታ የታየች ወጣት ሴት 'ይቺ ሙሽራ አሁን ያገባች ናት' ለማለት የሚስችል ተግባቦትን የሚፈጥር ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ባህላዊ አልባሳት እና ጌጣጌጥ አድርገው የሚታዩ ሴቶች የሙሽርነት ጊዜያቸው እንደሆነ ማህበረሰቡ በቀላሉ ያውቃል፡፡ ይህም ማለት ባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡ በማህበረሰቡና በለባሹ መካከል ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ተግባቦትን የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘውምአፀደ (2003) እና Wilson (1986) አልባሳቱ ለባሹን እና ማህረሰቡን የሚያግባቡት ኢ-ቃላዊ(verbal) በሆነመንገድበመሆኑ ምክንያት አልባሳት እና ጌጣጌጥ ልክ እንደቋንቋ ሁሉአንድን ማህበረሰብ ለመግለፅ በዋናነት የሚያገለግሉ ናቸው ሲሉ ገልፀውታል፡፡

## 4. መደምደሚያና ይሁንታ

### *4.1. መደምደሚያ*

ይህ ጥናት የተከናወነው ሶስት ዋና ዋና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ "የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ምን አይነት ባህላዊ አልባሳትንና ጌጣጌጥን ይጠቀማል?" የሚል ሲሆን በዞኑ በተለይ ናሙና የተወሰደባቸው ወረዳ ማህበረሰቦች የተለያዩ ባህላዊ አልባሳትን (እንክርት፣ሙሉ ሸንሸን፣

ጉርድ ሽንሽን፣ አርባ ሽንሽን፣ ጋቢ፣ ወንጨሬ፣ የጉልበት ሱሪ እና ፎጣ) እና ጌጣጌጦችን (ባውንድ፣ መንታ ድሪ፣ ድርብ ሽርብ ድሪ፣ ጥምዝ ድሪ፣ አምባር እና አልቦ) በተለያዩ አውዶች እየተጠቀመባቸው እንደሆነ በዚህ ጥናት ተመላክቷል። እነዚህ አልባሳት ከጾታ አኳያ ሲታዩ ሴቶች የሚለብሱት አልባሳትበአብዛኛውማለትይቻላል አንድ ወጥ ከላይኛው እስከታችኛው የአካል ክፍል የሚሸፍኑ ሲሆኑ ወንዶች የሚለብሱት ደግሞ በአብዛኛው ከወገብ በላይና ከወገብ በታች በሁለት የተከፋፈሉ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው የጥናቱ ጥያቄ "የምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ በባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡእንዴትራሱንይገልፃል?" የሚል ነው። በዚህ ጥናት እንደተመላከተው የዞኑ ማህበረሰብ ያለውን ማህበራዊ፣ መንፈሳዊ እና ምጣኔያዊ ገጽታዎች በአልባሳቱና በጌጣጌጡ ይገልጻል።እንዲሁም የማህበረሰቡ ባህላዊ አልባሳት ጌጣጌጥ ከፍተኛ ማህበራዊ ትስስር እንደሚፈጥሩና በማህበረሰቡና በለባሹ መካከል ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ተግባቦትን የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ከጥናቱ ውጤት ማረጋገጥ ተችሏል።

ጥናቱ የመለሰው የመጨረሻው ጥያቄ "በምስራቅ ጎጃም ማህበረሰብ ውስጥየአልባሳቱና የጌጣጌጡትዕምርትምንይመስላል?" የሚል ሲሆን በዞኑ ማህበረሰብ ዘንድ አገልግሎት ላይ እየዋሉ ያሉ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥለህይወት ምዕራፍ መግለጫ፣ ለእድሜ እርከን ማሳያ፣ ለማህበራዊኑሮደረጃ፣እና ስለመንፈሳዊ ኑሮውና ስለማህበራዊ ሁነቶቹ ማሳወቂያ ትዕምርቶች መሆናቸውን ከዚህ ጥናት ውጤት መገንዘብ ይቻላል።

*4.2. ይሁንታ*

ከጥናቱ ውጤትና ሂደት በመነሳት የተወሰኑ የይሁንታ ሃሳቦችን ማቅረብ ይቻላል። ይህ ጥናት የተከናወነው በምስራቅ ጎጃም ዞን በሚገኙ የተወሰኑ ወረዳዎች ላይ ብቻ ነው። ስለሆነም ከባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ስፋትና ውስብስብነት አኳያ በዚህ ዘርፍ ላይ ፍላጎት ያላቸው ተቋማት እና ምሁራን ጉዳዩን በስፋትና በጥልቀት ቢያጠኑት።

ከዚህ በተጨማሪ የአገራችንንም ይሁን የምስራቅ ጎጃምን ባህላዊ አልባሳት ማጥናት በተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎ የሚታዩ "ባዕድ" የአለባበስ ሥርዓቶችን መልክ ለማስያዝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል። በመሆኑም ያገባኛል የሚሉ ተቋማት እና ግለሰቦች ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሥርዓት ባለው መንገድ በሃቀኛነት እየተጠኑ ለሰፊው ህዝብ የሚተዋወቁበትንና አገልግሎት ለመስጠት ዋና አማራጭ ተደርገው የሚወሰዱበትን ስልት በማዘጋጀት በስፋት ሊሰራ ይገባል።

## ማጣቃሻዎች


Baatshwana, L.(1965). *World Costumes.*New York: The Macmillan Company.

Clark, G. (1986). *Symbols of excellence*. London: Cambridge University Press.

CSA [Central Statistics Authority].(2007). *Population and housing census.* Ethiopia: Addis Ababa.

Gracia, M. (2008).Communicating through clothing: The meaning of clothing among Hispanic women of different levels of acculturation.College of communication; Florida University.

KaiserH. (2004). *Cultural cloths: Functions, ideas*. Wisbaden: Frant steiner verlag Gmbh.

Lurie, A. (1981). *The language of clothes*. New York: Random House Inc.

Oestingaard K. (2002). A guide to th study of folklore: An introduction. Boston: Boston Book and Publisher

Prown, J. (1982). *Mind in matter: An introduction to material culture theory and method.*Retrieved from http://www.jstor.org/stable/11807661 on January/2016.

Sims, H., & Stephen,G. (2005). *American material culture: The Shop of things around us*. Bowling Green State: Bowling Green State University Popular Press.

Twigg,S. (2007). *Customary cloths: practices and conceptions*. London: Cambridge Univeristy Press.

Wilson, W. (1986).Documenting folklore. In E. Oring (edt) *Folk groups and folklore genres: An introduction*. Utah State University Press.

Woodward, I. (2007). *Understanding material culture*. Los Angles: SAGE Publication.

Yoder, D. (1972). *Folk costume, folklore and foklife: An introduction*. University of Chicago.

ሰይድ ይማም፤ (2002 ዓ.ም)።*በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ*። የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አመልማል ተሻለ፤ (2004 ዓ.ም)።*በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ-ጥናት*። የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አያል አድማሱ፤ (1992 ዓ.ም)።*የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ*። የባችለርዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አፀደ ያረጋል፤ (2003 ዓ.ም)።*የኮንሶ ሃገረሰባዊ አልባሳት እና ጌጣጌጦች፡- ገላጭ-ተንታኝ ጥናት*። የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍናፎክሎር ክፍለትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ፡፡

የኔዓለም አረዶ፤(2000 ዓ.ም)። *የአርሲ ሴቶች ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብ ሀሰሳ ወረዳዎች*። የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ያለውእንዳወቀ፤ (1998ዓ.ም)።*የምርምርመሰረታዊመርሆዎችናአተገባበር*። ባህርዳር፤ባህርዳርዩኒቨርሲቲ።

ያሬድ ተፈራ፤ (2002 ዓ.ም)፡፡*በሰቆጣና በአበርገላ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶችየአለባበስና አጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች*። የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።